# <u>ወያኔ ትግራይን ለመገንጠል ከሕዝቡ ሀሳብ እየሰበሰበ ነው!</u>

ወያኔ ከበረሀ ጀምሮ የተነሳበትን ሀገር የመበታተን እቅዱን በተግባር ለመተርጎምና ትግራይ ሪፑብሪክን ለመመሥረት የሚረዳውን የመጀመሪያ ስራ ለመስራት በሕዝቡ ውስጥ የሐሳብ መሰብሰብ ስራ ጀምሯል ። ከሕወሓት ስብሰባ ውሳኔ በኃላ የተጀመረው የመገንጠል ሒደት ጅማሮ አስመልክቶ የአረና አመራር አምዶን ይህን ፅፏል።
የትግራይ ባለስልጣናት ህዝቡን እየሰበሰቡ “ትግራይ ከኢትዮጵያ ብትገነጠል ምን ይመስላችኋል?” እያሉ አስተያየት እያሰባሰቡ እንደሆነ ከወደ ትግራይ ከውስጥ የሚመጡ መርጃዎች ያመለክታሉ።


(ቲ.ህ.ሓ.ኤ.ጽ)
የትግራይ ህዝብነፃ ኣውጪድርጅት
የካቲት ወር 1968 ዓ/ም

ሀ- <u>ዓላማውና ሥራው።</u>
የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፐሪያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንኡሳ ከበርቴያ ዊ. ጠንኝ ሰውም ነው። ስለዚህ የአብዮታዊው ትግል ዓላማ ከበጎንታዊ ሥርዓትና ከኢምፐሪያሊዝም ነፃ የሆነ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ይሆናል።

**“ትግራይ ከኢትዮጵያ ብትገነጠል ምን ይመስላቹሃል?”**

ሰሞኑ ከህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ስብሰባ ተያይዞ በየገጠር ወረዳውና ቀበሌዎች ኢንፎርማሊ እየተስፋፋች ያለችው ወሬ ናት።
የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ስብሰባ ተከትሎ ስለ ትግራይ መገንጠል በወሬ መልክ ህዝቡን እየጠየቁት ያሉት ለምን ይሆን?
ህወሓት ስትመሰረት የመጀመርያ 6 ወር ፕሮግራእዋ “ትግራይ ሪፐብሊክ” መመስረት የሚል እንደነበረ የሚታወቅ ነው። የድሮ ሃሳባቸው ከ42 ዓመት መልሰው ኣጀንዳ እንዲያደርጉት ያስገደዳቸው ምክንያትስ ምን ይሆን?